


ሚያዚያ 24/2001

# ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የተሰጠ ወታደራዊ መግለጫ

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር፤ ሰራዊት በሰሜን ጎንደር በዳንሻ እና በጠገዴ በሚገኝ አዲ ዳጉሳ በተባለ አካባቢ መጋቢት 30 ቀን 2001 ዓ/ም በወያኔ ልዩ ሃይል ሰራዊት ላይ በወሰደው ወታደራዊ የማጥቃት እርምጃ 14 ወታደሮችን ካሴ ከተባለ መሪያቸው ጋር በመደምሰስ የተለያዩ መሳሪያዎችንና ወታደራዊ ቁሳቁሶችን መማረካቸውን የኢሕግ ወታደራዊ መምሪያ አስታውቋል።

በእለቱ ጀግኖች አርበኞች ለአካባቢው ነዋሪዎች የኢሕግን አላማና ግብ አስመልክቶ በቂ ገለጻ የሰጡ ሲሆን ገለጻውንም ተከትሎ 20 የሚሆኑ ወጣቶች ኢሕአግን ተቀላቅለዋል። ወያኔ በንጹሃን የአካባቢው ነዋሪዎች ላይ ለድርጅቱ ስንቅና ትጥቅ ታቀብላላችሁ በሚል የውሸት ክስ እንግልትና ስቃይ እያደረሰባቸው ይገኛል።

ይህ በዚህ እንዳለ በቅርቡ አንድ ከፍተኛ የወያኔ ሹም በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር እንቅስቃሴ በቁጥጥር ስር እንዳዋሉት በወያኔ ፓርላማ ወስጥ ሪፖርት ማቅረባቸው ይታወሳል።

**አንድነት ሃይል ነው!!!**
**የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር**

Email: info@eppfonline.org:      Website: www.eppfonline.org